# ታላቅ አዎንታዊ ንቅናቄ ሊፈጥር የሚችል እርምጃ!

ኃይሌ ተረፈ 09-10-14

በማንውም የመንግስት አስተዳደር ውስጥ የመንግስት ሰራተው ሚና ቁልፍ ነው፡፡ የአስተዳደሩ ጥንካሬ የሚለካውም በዚሁ አካል ውጥታማነት መሰረት መሆኑም በብዙዎች ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ህዝብ የሚሻውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት በሚል በአስተዳደሩ የሚቀየሱት ማናቸውም ፖሊሲዎች በግንባር ቀደምትነት የሚተገበሩት አስተዳደሩ ቀጥሮ በየዘርፉ ባሰማራቸው ሰራተኞቹ አማካኝነት ነው፡፡

እነዚህ በተለያየ ፊና የተሰማሩት የመንግስት ሰራተኞች በስራችው ደስተኞች ካልሆኑና የተሰጣችውን ሃላፊነት ለመወጣት የላቀ ተነሳሰነት ከጎደላቸው ህዝብ በሚጠብቀው አገልግሎት ላይ አደጋ ይከሰታል፤ ይህ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ከቆየ በመንግስት የማስተዳደር አቅም ላይ ጥያቄ በማጫር በመንግስትና ህዝብ መካከል ቅራኔን ሊያስከትልና መልካም በሆነው የፖለቲካና ኢኮኖሚ አስተዳደር ሂደት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ይልቃል ተብሎ የሚገመት የመንግስት ሰራተኛ ወይም ሲቪል ሰርቫንት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ባሉ የመንግስት አስተዳደራዊ መዋቅሮች ተሰማርቶ ይገኛል ይባላል፡፡ ይህ የሰራተኛ ቁጥር ከ20 ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ሲወዳደር በእጅጉ የሚለልጥ ነው፡፡

በአገሪቱ አዲስ የፖለቲካ አስተዳደር በተመሰረተበት በ1983 ዓም የመንግስት ሠራተኛው በጥቂት መቶ ሺዎች ብቻ የሚቆጠር እንደነበር ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ከ20 ዓመታት በፊት የነበሩት የመንግስት አስተዳደሮች በጠባብ መሰረት ላይ የተዋቀሩ ከመሆንቸውም በተጨማሪ በብዙዎቹ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል በመድረስ የሚገባውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የማያቀርቡ መሆናቸውን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ የመንግስት ሰራተኛው ቁጥር በከፍተኛ መጠን እያደገ መምጣቱ አንድ ትልቅ ፖለቲካዊ አንደምታን ያነገበና ከዜጎች ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም ጋር ጠንካራ ቁርኝት ያለው እውነትን ያሳያል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከ20 ዓመታት በፊት በተወሰኑ ከተሞች ብቻ የተወሰነው የመንግስት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአገልግሎት ሽፋን በአሁኑ ወቅት ከከተሞች አልፎ በቀላሉ ሊደረስባቸው ያዳግቱ ወደነበሩት ፍጹም ገጠር ቀበሌዎችና መንደሮች ድረስ በመዝለቅ እየተስፋፉ መምጣቱ የመንግስት ሰራተኛው ቁጥር እንዲያድግ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ሊጠቀስ ይችላል ብዬ አስባለሁ፡፡

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ስራ ላይ የዋለውን ፌዴራላዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተዳደራዊ መዋቅር ተከትሎ እየሰፋ የመጣው የመንግስት አስተዳደርና በዚህም አማካኝነት የሚሰጠው የህዝብ አገልግሎት ለዘመናት ተዘንግተው የቆዩ አያሌ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚፈልጉትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት አገልግሎት እንደዚሁም በአገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

ከዚህም ሌላ ከዚህ በፊት በመጠን እጅግ ውስን የነበረው የመንግስት የልማትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋታቸው፤ ለህዝብ ህይወት መሻሻልና ደህንነት መረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ የአገልግሎት ዘርፎች መፈጠራቸው የመንግስት ሰራተኛው ቁጥር እንዲጨምር አድርጎታል ብሎ ለመናገር ያስችላል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስታዊ አስተዳደርና የልማት ተግባራት በቁጥርም ሆነ በዓይነት እየሰፉ መምጣት መንግስት በየዓመቱ ለህዝብ አገልግሎት መጠናከርና ልማት መስፋፋት የሚመድበውን በጀት መመልከትም ሌላው ማሳያ ሊሆን ይቻላል፡፡ ከ20 ዓመታት በፊት በእጅጉ አነስተኛ የነበረው ዓመታዊ የመንግስት ወጪ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ እመርታ በማሳየት ዘንድሮ ከ180 ቢሊዮን ብር ልቋል፡፡

አዲሱ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት ሰራተኛውን በመላው የአገሪቱ ክፍሎች በማሰማራት ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን ግን የለበትም፡፡ ምክንያቱም ከማእከል ጀምሮ እጅግ ርቀው እስከሚገኙት ገጠሮች ድረስ በተዘረጋው የመንግስት አስተዳደር በተለያየ የሙያ መስክ የተሰማራው ሰራተኛ ህዝብንና መንግስትን በቅንነት፣ በብቃትና በታማኝነት የሚያገለግል፤ ውጤታማ በመሆንም የህዝቡን ህይወት ለማሻሻል ደከመኝ ሳይል ዘውትር የሚተጋ ይሆን ዘንድ የግድ ይላል፡፡

እናም የዚህ ዓይነቱን የመንግስት ሰራተኛ ለመፍጠር ባለፉት ዓመታት ተከታታይና እስካሁንም ድረስ ያልተቋረጠ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን እንደአንድ የመንግስት ሰራተኛነቴ በቅርብ የማውቀው እውነት ነው፡፡ በዚህ ረገድ በርካታ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ መርሃ ግብሮች የሙያ አቅምን ከማጠናከር ጀምሮ የስራ ተነሳሽነትንና የህዝብ አገልጋይነት ስሜትን ለማጎልበት የሚያስችል ድባብን መፍጠርን ጨምሮ ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያካተቱ ናቸው፡፡

ከእነዚህ መርሃ ገብሮች መካከል ቁልፍ ሊባል የሚችለው ጠንካራና አቅሙ የተገነባ ሲቪል ሰርቫንት መፍጠር ይቻል ዘንድ በመንግስት የተቋቋመው ከፍተኛ የትምህርትና ስልጠና ተቋም ይጠቀሳል፡፡ ከኮሌጅ ደረጃ ተነስቶ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በመባል የሚጠራው ይህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በስራ ላይ የሚገኙትን የመንግስት ሰራተኞችን በማሰልጠን የተለያየ ደረጃ ያላቸው ሙያተኞችን በማፍራት ላይ ነው፡፡

ከተቋሙ እየወጡ ያሉት ባለሙያዎችም እስከ ገጠር ድረስ በመዝለቅ ህዝብ ከመንግስት የሚሻውን አገልግሎት በቅርበት ሆነው በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ መንግስት የሚቀይሳቸውን የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞችንም ህዝቡን በማስተባበር በመፈጸም ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ህዝቡ በእውቀት ላይ የተመሰረተና ጥራቱ የተሻሻለ አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ በተቻለ መጠን ተመቻችቷል፡፡

ሌላው መንግስት ሰራተኛውን በብቃትና በስፋት መጠቀም ይቻለው ዘንድ የወሰደው እርምጃ የመንግስት ሰራተኛውን ጉዳይ የሚከታተል ራሱን የቻለ የሚኒስቴር መስሪያቤት በአዋጅ መቋቋሙን የተመለከተው ነው፡፡

መስሪያ ቤቱ ሰራተኛው የመንግስትን አገራዊ የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በጥልቀት ተገንዝቦ በብቃት መፈፀም እንዲችል ዓለም ዓቀፋዊ ከሆኑ ሳይንሳዊ የአሰራር ስልቶች ጋር ሰራተኛውን ከማስተዋወቅ ባሻገር በሰራተኛው መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር፣ ማንኛውም ዓይነት የስራ ዕድገት፣ ጥቅማጥቅሞችና ሌሎች መሰል ዕድሎች እያንዳንዱ ሰራተኛ በሚያሳየው የአፈጻጸም ውጤታማነት እንዲሆን የሚያስችል ስርዓትን በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡

ይህም ህዝብ ከመንግስት የሚሻውን የአገልግሎት ጥራትና ስፋት ከማሳደግ ጎን ለጎን የሰራተኛውን ተነሳሽነት ያጠናክራል፤ መብቱ እንዲጠበቅለትና ግዴታውን በአግባቡ ተገንዝቦ ሃላፊነቱን እንዲወጣም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሲቪል ሰርቪሱን ለማጠናከር ሌላው ስራ ላይ የዋለው የመንግስት ተግባር እጅግ ኋላ ቀርና ደካማ የነበሩትን የተለያዩ የመንግስት ተቋማትን ዘመናዊ ቁመና ለማላበስ የተወሰደው እርምጃ ነው፡፡ ለረጅም ዓመታት ተገቢ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት እንኳ በወጉ ያልተደራጁት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአሁኑ ወቅት ዘመናዊና ምቹ ህንፃ ከመገንባት ባሻገር ብዙዎቹ ዘመኑ በሚጠይቀው ቴክኖሎጂ በመደራጀት ለስራና አገልግሎት አሰጣጥ ምቹ የሆነ ድባብ በመፍጠር ላይ ናቸው፡፡

እነዚህ እርምጃዎች ከዚህ በፊት እጅግ ኋላ ቀርና አድካሚ በሆነ እንደዚሁም ለስራና ሰራተኛው በማይመች ሁኔታ ይከናወኑ የነበሩ የእለት ተእለት ስራዎች ቀልጣፋና ቀላል እያደረጉት መሆናቸውን እየታዘብን ነው፡፡ ይህም ህዝብ ከመንግስት የሚጠብቀውን አገልግሎት ቀልጣፋ፣ የሰራተኛውን የስራ ተነሳሽነት፣ ውስጣዊ ስሜትንና ውጤታማነትንም እያሻሻለው መሆኑን በግሌ ለመመስከር እደፍራለሁ፡፡

ሰሞኑን ለመንግስት ሰራተኛው የተደረገው የደምወዝ ማሻሻያ ጉዳይም ከእነዚህ ተከታታይ የሆኑ እርምጃዎች ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳ የደምወዝ ማሻሻያ ሊደረግ መሆኑን መንግስት ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የጭማሪውን መጠን በተመለከተ ያለምንም ማጣራት ካፒታል በተሰኘው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋዜጣ ላይ የወጣው እጅግ የተጋነነና የተሳሳተ ዘገባ በሰራተኛው ማህበረሰብ ላይ መጠነኛ ግራ መጋባትን የፈጠረ ቢሆንም ጭማሪው የሰራተኛውን ወርሃዊ ገቢ በተወሰነ መልኩ እንደሚያሳድገው እርግጥ ነው፡፡

የዘንድሮው ጭማሪ ከሶስት ዓመታት በፊት ከተደረገው ተመሳሳይ ጭማሪ ጋር ሲነጻጸር እንኳ መጠኑ ከፍ ያለ መሆኑን ስንገነዘብ በተወሰነ መጠን የሰራተኛውን የኢኮኖሚ ጫና ያቃልለዋል ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

የተጠቀሰው ጋዜጣ የደምወዝ ጭማሪውን መጠን በማስመልከት የቀረበው አሃዝ እጅግ የተጋነነና ይተግበር ቢባል እንኳ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በከፍተኛ ደረጃ የሚያመዝን

መሆኑን የኢኮኖሚ ሙያተኞች ጭምር የሚገልጹት እውነታ ነው፡፡ በጋዜጣው ላይ እንደተመለከተው ዓይነት ከመቶ ፐርሰንት በላይ የወርሃዊ ደምወዝ ጭማሪ እንኳን ኢኮኖሚያቸውን እንደአዲስ በመገንባት ላይ ባሉት ኢትዮጵያን የመሰለ አገር ቀርቶ በልፅገዋል በሚባሉት አገራትም የማይሞከር የተሳሳተ ምጣኔ ኃብታዊ ቀውስ መሆኑንም የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በፊት ለመግለፅ እንደሞከርኩት በአሁኑ ወቅት የመንግስት ሰራተኛው ቁጥር ከሚሊዮን በላይ ልቋል፡፡ መንግስት ለዚህ ሰራተኛ የደምወዝ ጭማሪ ሲያደርግ በገንዘብ አቅሙ ላይ ጫና ማሳደሩ አይቀርም፡፡ ይህም ሆኖ ግን መንግስት ጭማሪውን ያደረገው አጠቃላይ አቅሙንና የአገሪቱን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ባለስልጣናቱ በሰጡት መግለጫ አሳውቀውናል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ላለው ለዚህ የህብረተሰብ ክፍል የደምወዝ ጭማሪ ሲደረግ ሌላም በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ መኖሩን መዘንጋት አይገባም፡፡

ከአንድ ሚሊዮን የሚልቀው ዜጋ ወርሃዊ ገቢው ሲጨምር በአገሪቱ አጠቃላይ ምጣኔ ኃብታዊ ስርዓት ውስጥ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የገቢ መጠን ሲጨምር የሰራተኛው የመሸመት ፍላጎትም በዛው መጠን ይጨምራል፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ በአገራዊው ገበያ ውስጥ ባለው አቅርቦት ላይ ጫና ስለሚፈጥር የሸቀጥና አገልግሎት እጥረትን ያስከትላል፡፡ ይህንን ተከትሎም የዋጋ ንረት ይከሰታል፡፡

ይህ ደግሞ ለሰራተኛው ያገኘውን ተጨማሪ ወርሃዊ ገቢ መና ከማስቀረት ባለፈ የአገሪቱን ጤናማ የገበያ መስተጋብር ሊያናጋውና አለመረጋጋት ውስጥ ሊከተው ይችላል፡፡ እናም ከመንግስት መግለጫዎች መረዳት የሚቻለው ጭማሪው የዚህ ዓይነቱን ምጣኔ ኃብታዊ ችግር ለመከላከል በሚያስችል ጥናት ላይ ተመስርቶ የተሰላ መሆኑን ነው፡፡

በእኔ እምነት ግን ከደምወዝ ማሻሻያው ባለፈ የሰራተኛውን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማጠናከር በመንግስት እየተወሰዱ ያሉት ሌሎች እርምጃዎች ትልቅ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሰሞኑን በመንግስት ባለስልጣናት ሲነገር እንደሰማነው የመኖሪያ ቤት፣ የትራንስፖርት አገልግሎትና መሰረታዊ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ የሚቻልበት መንገድ እየተመቻቸ ነው፡፡

መንግስት ያሰባቸውና በተግባርም የጀመራቸው እነዚህ የድጋፍ ማእቀፎች ከወርሃዊ የደምወዝ ጭማሪው ይልቅ ሰራተኛውን ኢኮኖሚያዊ አቅም በዘላቂነት ሊያጠናክረውና ህይወቱንም በአግባቡ እንዲመራ የሚያስችሉት ናቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ለዚህም ምክንያት አለኝ፡፡ በአብዛኛው ከተሞች አካባቢ የሚገኘው የመንግስት ሰራተኛ ትልቅ የሚባለው ወጪ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ወጪ ነው፡፡ በብዙ ጥናቶች እንደተረጋገጠው በተለይ በአዲስ አበባ ዓይነቱ ከተማ ውስጥ የሚኖረው የመንግስት ሰራተኛ ከግማሽ ያላነሰው ወርሃዊ ገቢ የሚውለው ለቤት ኪራይ ነው፡፡

ከቀለብ ጋር የተያያዘው ወጪም በሁለተኝነት ደረጃ ላይ ሊቀመጥ የሚችል የሰራተኛው ኢኮኖሚ ጫና ምክንያት የሆነ ችግር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ጋር አንዳችም ግንኙነት በሌላቸው መሰረቶች፤ ሌላ ጊዜም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚፈጠሩ የዋጋ ግሽበቶች ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ የሰራተኛውን ገቢ በእጅጉ እየተፈታተኑ የሚገኙ የቆዩ ችግሮች ናቸው፡፡

የትራንስፖርት ችግርም ሌላው የሰራተኛው የእለት ተእለት ራስ ምታት መሆኑን ማስረዳት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

እናም ከእነዚህ ማእቀፎች መካከል መሰረታዊ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሰራተኛው ማቅረብን ያለመው ማእቀፍ በተወሰነ መልኩ ስራ ጀምሯል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች ስራ የጀመሩት የሸያጭ ማእከላት በመንግስት ሰራተኛው ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የወጪ ጫና ከማቅለል አኳያ ትልቅ ሚና በመጫወት ላይ መሆናቸውን ብዙዎቹ ተጠቃሚዎች በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡ የሽያጭ ማእከላቱን ቁጥር ለማስፋትና በማእከላቱ የሚቀርቡትን የሸቀጥ ዓይነቶችንም ለማብዛት መንግስት አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑም እየተነገረ ነው፡፡

ሌላው በመጪው ዓመት መስከረም ወር ላይ ይጀምራል ተብሎ የሚጠበቀው የመንግስት ሰራተኞች የድጋፍ ማእቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎትን ይመለከታል፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ በሚገኘው ሰራተኛ ላይ የዘውትር እንግልትና አላስፈላጊ ወጪ ምክንያት የሆነውን የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ለማስወገድ የተቋቋመው ድርጅት ስራውን ለመጀመር አስፈላጊውን ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ ነው፡፡

ይህም በሰራተኛው ወርሃዊ ላይ በትራንስፖርት ወጪ የሚፈጠረውን ጫና ሙሉ በሙሉ ሊያቃልለው ይችላል የሚል እምነት አሳድሯል፡፡

ከሰራተኛው ገቢ ጋር የተገናዘበ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለመንግስት ሰራተኛው ለማመቻቸት ማእቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩም ለሰራተኛው ትልቅ እፎይታን የሚፈጥር እንደሆነ በሰራተኛው ዘንድ እየተገለፀ ነው፡፡ ሰሞኑን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ጽህፈት ቤት በ20/80 የቤቶች ልማት ፕሮጀክት 20 በመቶ የሆኖነው ለሰራተኛው የሚውልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ላይ መሆኑን አስታውቋል፡፡

በእኔ እምነት መንግስት በስሩ ለሚያስተዳድራቸው ሰራተኞቹ የቀረፀውና ወደተግባርም እየለወጣቸው ያሉት የድጋፍ ማእቀፎች ከወርሃዊ የደምወዝ ማሻሻያ በላቀ የሰራተኛውን የኢኮኖሚ ጫና ከማቃለል አኳያ ትልቅ ትርጉም አላቸው፡፡

ማእቀፎቹ በእጅጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች ላይ ያነጣጠሩና የሰራተኛውን ህይወት እየተፈታተኑ ለእድገቱ ማነቆ በሆኑበት ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ትልቅ ማህበራዊ አንደምታ ይኖራቸዋል ብዬም አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም ድጋፎቹ ሰራተኛውን ብቻ ሳይሆን ልጆቹን ጨምሮ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን በብዙ ሚሊዮን የሚገመቱ ሌሎች ዜጎችንም ህይወት ከማሻሻል አንፃር የራሱ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ መገመትም ይቻላል፡፡

እነዚህ የድጋፍ ማእቀፎች ተግባራዊ ከሆኑ ከአንድ ሚሊዮን የሚልቀው የመንግስት ሰራተኛ የተጣለበትን የእለት ተእለት የመንግስትና የህዝብ ኃላፊነት በትጋትና በባለቤትነት ስሜት ለመወጣት ይችል ዘንድ አዲስ መነሳሳትንና ጉልበትንም ይፈጥሩለታል፡፡ ከዚህም አልፎ ማእቀፎቹ መንግስት ላለፉት ዓመታት መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር የጀመረውን ዘርፈ ብዙ ጥረትን የሚያግዘው መሆኑንም ማመልከት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ሰራተኛው የእለት ተእለት ችግሩን ከማሰብና ከመብሰልሰል ወጥቶ ስራውን በሙሉ ልቡና ተነሳሽነት ሲያከናውን ህዝብ ከመንግስት የሚጠብቀው የአገልግሎት ጥራት ይሻሻላል፤ የመንግስት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚፈለገው ፍጥነትና አግባብ ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፡፡ በዚህም የተነሳ በመንግስትና ህዝብ መካከል ጤናማና በመተጋገዝ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ግንኙነት ይፈጠራል፡፡

እናም እንደአንድ የመንግስት ሰራተኝነቴ ከወምወዝ ማሻሻያው በበለጠ የሰራተኛውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከማቃለል አንፃር ትልቅ ግምት የምሰጠው ከላይ ለተዘረዘሩት የድጋፍ ማእቀፎች መሆኑን የምገልፀው በታላቅ ደስታና ተግባራዊነታቸውም እውን እንደሚሆን ጥልቅ እምነትን ይዤ ጭምር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ስሜት ያደረብኝ ደግሞ እንዲያው የሚነገሩትንና የሚሰጡትን መግለጫዎች ብቻ ተንተርሼ ሳይሆን ከመግለጫዎቹ ባለፈ ተጨባጭ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ በመቻሌ ጭምር ነው፡፡

በበኩሌ የመንግስት እርምጃ በመንግስት ሰራተኝነቴ እንድኮራና በስራዬም አዲስ ኃይልና ጉልበት እንድፈጥር የተጣለብኝን ኃላፊነትም በዚሁ አዲስ ኃይልና ጉልበት እንድወጣ ያደርገኛል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የዚህ ዓይነቱ መነቃቃት በመላው የመንግስት ሰራተኛው መንፈስ ውስጥ ይፈጠራል ብዬም አስባለሁ፡፡

አስተያየቴን መቋጨት ይቻለኝ ዘንድ አንድ ነገር ልበል፡፡ ሰሞኑን ይፋ የሆነው ዓይነት የደምወዝ ማሻሻያ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገትና አቅም ባገናዘበ ጥናትና በተሻለ መጠን ወደፊትም እንደሚቀጥል መንግስት አስታውቋል፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን በኢኮኖሚ ባለሙያዎች እምነት የሰራተኛውም ሆነ የመላው ዜጋ ህይወት በዘላቂነትና በአስተማማኝ መልኩ ሊሻሻል የሚችለው በደምወዝ ጭማሪ ብቻ አይደለም፡፡

ከዚህ ባሻገር አጠቃላይ የሆነ አገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ፣ አቅርቦትንና ፍላጎትን ያጣጣመ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ መገንባት ወሳኝ መሆናቸውን ጠበብቱ ይመክራሉ፡፡ እነዚህ ላይ አንድ የታዘብኩትን አዎንታዊ የመንግስት ተግባር ማንሳት እሻለሁ፡፡ ይህም የዋጋ ግሽበትን ይመለከታል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከስቶ ከነበረ የኢኮኖሚ ቀውስና በአገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተነቃቅቶ ይካሄድ ከነበረው የኢኮኖሚ እንቀስቃሴ ጋር በተያያዘ በአገራችን ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ተከስቶ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ይህንን በተለይም በሸቀጦች ላይ የተከሰተውንና 40 በመቶ ደርሶ የነበረው የዋጋ ግሽበት መንግስት በወሰዳቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ የፖሊሲ እርምጃዎች በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ወደአንድ

አሃዝ ማውረድ መቻሉ ኢኮኖሚው የተረጋጋ ድባብ ውስጥ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ያረጋገጠ ተግባር ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

የዚህ ዓይነቱ አዎንታዊ ውጤት ደግሞ የተረጋጋ ኢኮኖሚ ከመፍጠር ባለፈ የመንግስት ሰራተኛውን ጨምሮ በአነስተኛ ገቢ በሚተዳደረው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ትልቅ እፎይታን አስገኝቷል፡፡

ፈጣንና የተረጋጋ የኢኮኖሚ ልማት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ መሆኑንና የተያዘው መንገድም የሚያበረታታ መሆኑን በኢኮኖሚ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት የሚያካሂዱ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር አረጋግጠዋል፡፡

ይህ በአገሪቱ የተጀመረው የኢኮኖሚ መነቃቃትና እድገት አሁን ባለበት ፍጥነት ከቀጠለ የመንግስት ሰራተኛውን ጨምሮ መላው ዜጋ መካከለኛ ገቢ ካላቸው የዓለም አገራት ተርታ የሚሰለፉበት ወቅት ሩቅ አለመሆኑንም እነዚሁ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሌሎች አካላትም እየመሰከሩ ይገኛል፡፡

የዚህ ዓይነት ዜጎች በኢትዮጵያ እየተፈጠሩ ስለመሆናቸው ከወዲሁ እየተስተዋለ በመሆኑ እመርታው ሊጨበጥ የተቃረበ እውነት ነው የሚለው በብዙዎች እየተነገረ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ታዲያ የእኛ የመንግስት ሰራተኞች ሚና የማይለካ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ምንም እንኳ የተለያዩ ክፍተቶች አሁንም ድረስ ያሉ ቢሆንም በኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በሁሉም ዘርፍ ለተገኘው ድል የመንግስት ሰራተኛው ድርሻ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ እናም በተሰማራንበት ፊና ሁሉ ለአገራችን፣ ለህዝባችንና ለራሳችን ብለን የበለጠ ልንነቃና ልንተጋ ይገባል፡፡

የዚህ ዓይነቱን ስሜት መላበስ ይቻል ዘንድ ደግሞ ታዲያ መንግስት የሲቪል ሰርቪሱን ዘርፍ ለማሻሻል እየወሰዳቸው ያሉት ዘርፈ ብዙ እርምጃዎች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ በባለቤትነትና ብሄራዊ ሃላፊነት ስሜት መሳተፍ ከሰራተኛው የሚጠበቅ ቁልፍ ተግባር ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ መንግስት በተለያየ አቅጣጫ የሲቪል ሰርቪሱን ሁኔታ ለመለወጥ እየተገበራቸው ያሉት መርሃ ግብሮች ለውጥ እያመጡ ስለመሆናቸው ማስረጃ እያቀረብኩ መግለጽ እችላለሁ፡፡

በአገልግሎት አሰጣጥ፣ የመንግስትን የልማት ፕሮግራሞች በማስፈጸም ረገድ በርካታ የሚያበረታቱ ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን ህዝቡ ራሱ ምስክርነቱን በመስጠት ላይ ነው፡፡ ሆኖም ህዝቡ አሁንም ተጨማሪና ቀጣይነት ያላቸውን ለውጦች ይፈልጋል፡፡

በአገሪቱ ጠንካራ የመልካም አስተዳደር ሁኔታ እንዲፈጠር ከህዝብ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ጆሮ ያልነፈገው መንግስትም ከሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉ ቁልፉን መልካም አስተዳደር አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ከተለያዩ የመንግስት እቅዶችና ሌሎች የስራ ሰነዶች እንደዚሁም ከእለት ተእለት የመንግስት ተግባራት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ የመንግስት ሰራተኛ በተሰማራበት የስራ ዘርፍ ሁሉ ውጤታማ ለመሆን ከተጋ፤ ሊገኝ በሚችለው መልካም ውጤትም ተጠቃሚ የሚሆነው ራሱም ጭምር መሆኑን ከልቡ መቀበል ከቻለ ይህች አገር ያሰበችውን የመታደስ ራእይ እውን ታደርጋለች፡፡

በዚህ በኩል መንግስት ለሰራተኛው ጥቅም ሲል የቀየሳቸው የድጋፍ ማእቀፎች ታላቅ መነቃቃትን ይፈጥራሉና የዚህ ዓይነቱ የመንግስት እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት እያሳሰብኩ አስተያየቴን ቋጨሁ፡፡